## የስለጠና ግኘርና አጠቃቀምን በተመለከተ ፣

3 ዓይነት አጠቃቀም አለ ፡፡

1. In house skills development የሚባለው የመነግሥት ፖሊስን ፣ የአሰራር ሁኔታዎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ግንዛቤ ማስጨበጥ ወርክሾፖችና አጫጭር ስልጠናዎችን የሚያካትት ሲሆን በአንድ ሴሽን ለአንድ ሠልጣኝ በሚፈጅ ዋጋ የሚሰላ ነው ፡፡ ከደሞዝ በስተቀር ስልጠና የጽህፈት መሣሪያዎች፣ ውሎ አበልና ወዘተ ይሸፈናል ፡፡ በዚህ ስልጠና የሥ/አመራር ተቋም የሲ/ሰ/ኮሌጅ ፣ ዩኒቨርስቲዎች ወዘተ ሊካተቱ ይቸላል በቅድሚያ ግን በዕቅዱ የተካተቱና ዓለም ባንክ የሚያውቀው ሊሆን ይገባል ፡፡

2. Specialized Training የሚባለው እንደ IT network መዘርጋትና ጥገናዎች ፣ የሙያ ለውጥ የሚያመጡ ስልጠናዎች ወዘተ የሚያካትት ሲሆን ይህ በጨረታ ውድድር የሚከናወን ነው ፡፡ እንደ ምክር አገልግሎት ግኘር ከ 10000 የአሜሪካ ብር ወይም ከ 860000 የኢት/ብር በላይ ከሆነ የ TOR እና REP / request for proposal / ተቋሞች ፐሮፖዛል እንዲያቀርቡ የሚላክላቸው ደብዳቤ ሲሆን ከዓለም ባንክ N No objection N በቅድሚያ ማግኘት አለበት ፡፡

3. Generic training የሚባለው ደግሞ እንደ ስትራቴጂ አመራር ፣ የፋይናስ አመራር ፣ የአመራር ጥበብ የኮምፒውተር ዕቀውቀት ስልጠና ክትትልና ግምገማ ወዘተ የመሳሰሉ ስልጠናዎችን ፣ የሚመለከት ሲሆን የግል ተቋማት ፣ የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋማት ሆነው ህጋዊ የማስልጠን ሥልጣን የተሰጣቸው ተቋማት ሥልጠናውን ከሚፈለገው ኢ/ል/ሚ ወይም አ/ግ/ቢሮ ግልጽ በሆነ መስፈርት ተጠይቀው እንዲወዳደሩ ይደረጋል ፡፡ ዝቅተኛና ጥራት ያለው ዋጋ ያቀረበ በውድድር ተመራጭ ይሆናል ፡፡ መስፈርቱና የሥልጠናው ዓይነት ለ IDA በቅድሚያ ቀርቦ "No objection" letter ሊገኝ ይገባዋል ተቋማቱን Prequilfy ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡

   በዚህ መሰረት ከላይ የተገለጹት ለግንዛቤ ያህል እንጂ ዝርዝርና ጥንቃቄ ተሞላበት አሠራርና የሰነድ ዝግጅት የሚጠይቁ ናቸው ፡፡

## የበጀት ፍሰትና አጠቃቀም

በጀት ፍሰት የሚከናወን የበጀት ድርሻ ስለተሰጠ ብቻ ሳይሆን አፈጻጸምን ተከትሎ የሚፈጸም ነው ፡፡ በወቅቱ ሰርቶ በመመሪያው መሠረት ሪፖርት ፧የላከ በጀት ይለቀቅለታል ፡፡ ፈጥኖ የጨረሰ ተጨማሪ በጀት ማግኘት ይችላል ፡፡ በየሩብ ዓመት የሚላክለትን ያላጠናቀቀ በቀጣይ ከሚገኘው ዌም ላተናቀቀው በጀት ካለ በአፈጻጸም የተሻለ ለሆነው ይሰጣል ፡፡ ይህም የሚሆነው በዕቅዱ መሠረት 75 % ተግባራቱንና በጀቱን ያከናወነ የጠየቀውን በጀት የሚለቀቅለት ሲሆን ከተላከለት 25% እና በታች የተጠቀመ ደግሞ ቀድሞ ካቀደው ውስጥ 50 % ብቻ ይላክለታል ፡፡

ከፌደራል ፋ/ኢ/ል/ሚ በጀት በቀጥታ ወደ ክልሉ ፋ/ኢ/ል/ቢሮ የሚላክ ሲሆን ፋ/ኢ/ል/ማ/ቢሮ የፒስካፕ አካውንት ከፍቶ በጀቱን የሚያስተዳድር ሲሆን ሲጠየቅ አገልግሎት ለሰጠው አካል ውጪ ገንዘብ ለሌላ ተቋም አያስተላልፍም ፡፡

በጀት አጠቃቀምና ሪፖርት በአዲሱ የበጀትና የአካውንት ሪፎርም መሠረት የሚከናወን ነው፡፡

ፕሮጀክቶቹ ወደ ገንዘብ ጥያቄ የሚላኩት ከየደረጃው ፈጻሚ ሴክተሮችና ፕሮግራሞች ቤተክኒክ ኮሚቴና በአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ተረጋግጦ ከአ/ግ/ቢሮ ሲጠየቅ ነው ፡፡ በፌደራልም በተመሳሳይ አካል ሁንታ ካገኙ በኂላ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ነው፡፡

በፋይናንስ ቢሮ የተዘጋጁ አዲሱ የበጀትና የአካውንት ሪፎርም ሰነዶችና በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጀውን ግኘ መመሪያን በማጣጣም ለአገር ውስጥ ግገር መጠቀም ይገባል ። ለዓለም አቀፍ ግገር የዓለም ባንክ ህግ ተፈጻሚ ይሆናል ።

የፕሮግራሞቹን ተግባርና የፋይናንስ አፈጻጸም በተመለከተ በየጊዜው በዓለም ባንክና በረጂ ድርጅቶች እንዲሁም በእነሱ በሚቀጠሩ አማካሪዎች ግምገማ ይደረጋል ። በክልል ደረጃም በአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ፣ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮና በሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በየሩብ ዓመቱ ክትትል ይደረጋል ። የግምገማ መለኪያ አመልካቾችም በወጥነት ተዘጋጅተዋል ። የማንኛውም ግገር ክፍያ የሚፈጸመው በፋይናንስ ቢሮ ነው ።